ከታዛቢው (ኖርዌይ) 16.05.08

## ቀጣፊው አቶ መርሻ ውይስ ዶቼ ቬሌ?

በሜይ 15, 2008 የግንቦት 7ቱን ምክንያት በማድረግ የተኪያሄደዉን ሰልፍ አስመልክቶ በኖርዌይ የሚኖሩ የተለያዩ ድርጅቶች አባላትንና ደጋፊዎችን ያካተተ እንደነበርም የታወቀ ነው ግን በጣም የሚያስደንቅ በጣምም የሚገርም ውሸት በዶቼ ቬሌ ራዲዮ ጣቢያ ሲወራ ሰምተናል፣ በዚህ የሕዝብ አመኔታ ያለው ራዲዮ ጣቢያ ተጨባጭ ያልሆነና ለፖለቲካ ንግድ ሲባል ያልሆነዉን እንደሆነና ያልነበረዉን እንደነበረ ተደርጎ ሲነገር ሰምተናል፣ ይህም አቶ መርሻ ዮሴፍ በሌሉበት በሰልፉ ላይ እንደነበሩ ተደርጎ የውሸት ናዳ ሲለቀቅ ታዝበን ያለፍነው ጉዳይ ቢሆንም ሃቁ ግን በቦታው አለመኖራቸውን ነው የሰልፉ እድምተኞችም ሆነ የአገሩ ነዋሪውች የምናውቀው።

የሚያሳዝነው 30 ዓመት እውነትን ባወራ አፌ በድብቅ የዋሸሁት ስይቆጠር ቢሆንም በዚህች 2008 በስተርጅና በይፋ ብዋሸ የሚቆጥርብኝ የለም ነው መሰል ራሳቸውን የሰልፉ ተሳታፊ አድርገው ሲናገሩ መስማት እጅግ አሳፋሪ ነው።

በሌላውስ ዓለም ለሚኖረው አትዮጵያዊ ለፖለቲካ ገበያ ሲባል መዋሸቱ ደህና ግን የኖርዌይን ኢትዮጵያዊ ምን ያህል ቢንቁ ነው አንጋፋው እንዲህ ባልነበሩበት ቦታ ነበርኩ ብለው እንዲህ ያለው ውርደት ውስጥ ራሳቸውን የከተቱት፣ የበላችው ያቅራታል በላይ በላዩ ያጎርሳታል እንዲሉ ሎቱ ስብሃት ብለን ከማለት በስተቀር ሌላ ምን ይኗል፣ ተዓማኒንት ያላቸውንስ የሬዲዮ ጥቢያዎችንስ የውሸት ናዳ በመልቀቅ የገደልማሚቶ ማድረግስ ለምን? የነበሩትስ ኢሕአፓዎች እያሉ ያልነበሩት የ D አንጋፋ መሪ በማን ሴራ አማካኝነት ሊጠየቁና ለእንዲህ ቅሌት እንዲበቁ ተደረገ ለነገሩማ ትርፍ ተገኘ ተብሎ ነበር።

ሃቅ ያንቃል!